# የማይቀርለት ኢትዮጵያን እንደዩጎዝላቭያ የመበታተንዋ ጉዳይ፥ መሰረታዊ ምክንያቶች እና በሃላፊነት ተጠያቂዎቹ ለመለየት

ዶ/ር ብርሃነ ወልደሚካኤል (06-08-2021)

**ማስታወሻ**፥ ይሀ ኣጭር ድርሰት በኣማርኛ ለመጻፍ የተሞከረው - የቋንቋው ምልከት ኖሮን ሳይሆን ግን ምናልባትም የበዛ ሰው ያነበው ይሆናል ብለን ስላሰብን ነው። ፍላጎታችን፡ ለዘመናት በጦርነት የታመሰው የኢትዮጵያ ህዝብና የጐረቤት ህዝቦችም ጭምር ዘላቂ ሰላም እንዲያገኙ የሚያስችለው መንገድ ለመፈተሽ ነው። ህኸ ለማድረግ ግን ሃቅ በመደብቅ ሳይሆን የነበሩ ሁኔታዎች ብእውነተኛ መንገድ ሲነገሩ ብቻ መሆኑን እናምናለን። ይቅርታ የሚይስፈልገው ብይቅርት፥ ካሳ የሚያስፈልገው እንዲሁ በመካስ ነው ብህዝቦች መካከል የነበረ ቍስል ለማዳን የሚቻል የሚል እምነት ነው ያለን።

**ርእሰ ሃሳቦች**

ኢትዮጵያ ድንቅና ደግ ህዝብ የሚኖርበት ኣገር ናት። በቅን ኣገዛዝ ብትመራ ኖሮ፡ ኢትዮጵያ ካለችበት የድህነት ደረጃ በወጣች ነበር። እንደዝያ  በተፍጥሮ ሃብት የታደለች ኣገር ከዓለም በድህነት መለኪያዎች በታችኛው ደረጃ መገኘትዋ ይሚያሳፍር ነው።

ለኢትዮጵያ ዋና ጦስ የሆኑት ምክንያቶች መዘርዘር ከፍ ያለ ምርምር ይመያስፈልገው ጉዳይ መሆኑ ኣይካድም። ለመነሻ ያህል ግን እዚህ በኣጭሩ ለማመልከት እንሞክራለን።

የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሃፊዎች የኣንድ ከፊል የኢትዮጵያ ህዝብ ባልሆነ የበላይነት ኣስተሳሰብ እንዲሰክር ግዙፍ ተራ ተጫውተዋል።  ሁለተኛ ደረጃ ስማር የኣማርኛ ኣስተመሪ አንዲህ ሲል ተናገረ “ኣማራ ማለት ያማረ፡ ምርጥ የሆነ ሰው እንድማለት ነው” ኣለን። ክፍል ውስጥ የነበርነው ተማሪዎች ኣብዛኞቻችን  ኣማሮችም ኣልነበርንም ግን የኣስተማሪው ኣባባል ምን ዓይነት ኣስተሳሰ በታዳጊው ኣእምሮ እንደሚገባ ለመገመት ኣየስቸግርም። በሌላ ኣጋጣሚ ኣንድ የኣማራ ተወላጅ የሆነ ተማሪ በኢትዮጵያ የዘር የበላይነት ተርታ በሚያሳፍር ኣገባብ ገልጦታል። እኔ ኤርትራዊ ስለሆንኩ በኔ ፊት ሆኖት ትግሬ ብያስቀድምም፡ ሌላ ቦታ ቢሆንማ በሌላ መልኩ እንደሚያቀርበው ኣየጠራጥርም። ሌሎች ብዙዎች ኣዘግናኝ እና የድንቍርና መለኪያዎች የሆኑ ኣባባሎችም ነበሩ። ስለዚህ፣ ለእንደዚሁ ዓይነቶቹ ኣባባሎች በትምህርት ገበታቸው ለታዳጊ ልጆጅ የመስመር ማስያዣ ኣስተሳብ ማስተማር በተገባ ነበር።

ከዚህ የባሳም የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሃፊዎች በሃሰት “ኢትዮጵያ በእግዚኣብሄር የተመረጠች፡ በምጽሓፍ ቅዱስ ኣስራ ሶስት ግዜ የተጠቀሰች፡ ህያው ሆና የኖረች እና የምትኖር ኣገር ናት” ብለው ያለህፍረት ይሌለ ምስል መስጠት ተያይዘዉት ነበር። በዚሁ ዓይነቱ ትረካ የተሞሉ ኣጼ ሃይለስላሰ “ንጉሰ ነገስት ዘእምነገድ ይሁዳ” የሚል መዓርግ ለብሰው ፣ በቀጥታ ክንግስት ሳባ የተሳሰረ ይንግስነት ግኙኝነት እንዳላቸው ኣስመስለው ዘረዘሩት። በነገራችን ላይ ፡ ይኸ ንግስት ሳባ ከእስራኤላዊው ንጉስ ሰለሞን እንደወለድችና ምንሊክ የተባልው ልጅዋ በማይ በላ የሚባል ቦታ፡ የዛሬው ኣስመራ፡ ተወልዶ የኢትዮጵያ ንጉስ ሆነ የሚለው  የፈጠራ ልብ-ወለድ ታሪክ እንደ እውነት ተወስዶ በይፋ ኢትዮጵያ ውስጥ ሲነበብ ቆይቶዋል። እንግዲህ ጥራዝ ነጠቅ የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሃፊዎች እንዲህ ዓይነቱ የፈጠራ ተረት የኣማራ ህዝብ ታሪክ እንደሆነ ኣስመስለው በመጻፋቸው ድሃ ህዝባቸው ውስጥ `”ወተት ኣለኝ በሰማይ” ዓይነት የበላይነት ኣሰተሳሰብ ለማስያዝ ጥረዋል።

በነገራችን ላይ፣ የኣሁንዋ ኢትዮጵያ በቅርብ በንጉስ ምኒሊክ ሁለተኛ ዘመነ መንግስት፣ ግዛት በማስፋፋት

የተመሰረተች ኣገር ነች። የምጽሓፍ ቅዱሷ ኢትዮጵያማ ድሮ በኣግኣዝያኖች፣ የዛሬ ትግሬ እና ትግርኛ ተናጋሪዎች፥ ይተዳደር የነበረ ግዛት፡ በሰሜን እስከ ዳር የዛሬዋ ግብጽ፣ ብምስራቅ ቀይ ባህር ተሻግሮ የዛሬዋ የመን የሚያጠቃልል ሰፊ ኣገር የነበረ ነው። ኢትዮጵያ የሚል ቃል ያግሪክ ቃል ሆኖ የጥቁሮች ኣገር ወይም ኣረቦች ሃበሻ ብለው ይጠሩት የነበረ ህዝብ ይኖርበት የነበረ የኣግኣዝያኖች ኣገር ነው። እውነተኛው ታሪክ እንዲህ ሆኖ ሳለ፥ የኣክሱሙ የኣግኣዝያን ስልጣኔ ሆነ ተብሎ የትግሬዎች ታሪክ መሆኑ ሳይጠቀስ በኣጠቃላይ የኢትዮጵያ ታሪክ ኣስመስሎ በማቅረብ ብዙ የታሪክ ውስልትና ተሰርተዋል።

መገንዘብ የሚይስፈልገው ሌላ ጉዳይም ኣለ። ኢትዮጵያ ተራራማ ኣቀማመጥ የያዘች ኣገር  በመሆንዋ፣ በህዝቦችዋ መካከል ብዙ የእርስ-በርስ የመገናኘት ዕድል ኣልነበረም። ቢኖርምም በጦርነት ጊዜ በነፍጠኛ ሰራዊት ኣማካይነተ ለግዛት ማስፋፋት ተብሎ የሚደረግ ነበር።  የኣማራ ነፍጠኞች፣ የመንግስት ወኪሎች በመሆናቸው የወረሩት መሬት መዝረፍ እና ያገኙት ህዝብ በጭካኔ መግዛት መታወቅያቸው ነበር።

ትንታኔው ለማሳጠር ያህል፥ የኢትዮጵያ ህዝብ እርስ በርሱ በይበልጥ ለመተዋወቅ የቻለ በቅርቡ ቢኢሃደግ ዘመነ መንግስት ነው። በጠቅላይ ምኒስተር መለስ ዚናዊ ብልህነት፡ በኢትዮጵያ መስተንክር የእድገት ግስጋሴና የመግናኛ መስመሮች በብዛት የተዘረጋበት ዘመን ነበር።  በዚህ ምክንያት ይህዝብ ግኙኝነትም  እንዲሁ ብእጅጉ ለማደግ ችለዋል።

ነገሩ እንዲህ ህኖ ሳለ፥ ብትግሬዎች መሪነት ኢትዮጵያ ውስጥ የተከናወነው መስተንክራዊና ሁለንትናዊ እድገት የተወሰኑ የኢትዮጵያ ምሁራን (ልሂቃን) ሊደሰቱበት ሲገባቸው በኣንጻሩ የክፋት የጸረ አድገት ሴራቸው ሆነ ብለው ተያያዙት። እዚህ ላይ፥ ብምን ምክንያት ወደመቃወም መንገድ ሄዱ የሚል ጥያቄ መነሳቱ ኣይቀርም።

ኣስቀድሞ እንደተጠቀሰ፥ በተረት እና በሃሰት የተመሰረተ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ለተወሰኑ የኢትዮጵያ ልሂቃን ኣእምሮኣቸው ውስጥ የነበረው የበላይነት ኣስተሳሰብ በይበልጥ ከንቱ መሆኑ ሊገነዘቡት የቻሉ  በኢሃደግ ዘመነ መንግስት  ነው።  ኣግኣዝያኖች ብግዜኣቸው በጣም የሰለጠኑ፣ የሰፋ ግዛት ያስተዳድሩ የነበሩ፥ የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖቶች ብግዛታቸው እንዲስፋፋ ያደረጉ፣ ብንግድ ክብዙ ኣገሮች ይገናኙ የነበሩ የሰለጠኑ ህዝብ እንደነበሩ  ሊረዱ ቻሉ። ታድያ፣ በሃሰት የኢትዮጵያ ታሪክ ብለው ይወስዱት የነበረው፡ ኢትዮጵያ ከመፈጠርዋ በፊት የኣጋኣዝያን ታሪክ እንደነበረ ሆኖ ነው ያገኙት። በተጨማሪም፥ ብዙዎች በኢትዮጵያ ስም የሚጠሩ የባህል መታወቅያዎች መነሻቸው የኣግኣዝያን ባህል መሆኑን ሊገነዘቡ ቻሉ። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም የተባሉ ምሁር፡ ኣስቀድመው የኣማራ የባልይነት የሚል ኣስተሳሰብ የነበራቻው ሰው ነበሩ። ነገሩ በደንብ ሲረዱት ግን ኣንደዝያ ያልሆነ የበላይነት ኣስተሳሰብ ውሎ-ኣድሮ በኣማራ ህዝብ ላይ የሚያመጣው ከፍተኛ ኣደጋ በመረደት፣ `ኣማራ የሚባል ጎሳ የለም፡ ኣማራ የብዙ ጎሳዎች ክምችት ነው` በማለት ኣስቀመጡት።  ለጥቂቶች የኢትዮጵያ ልሂቃን (ኣሞሮች እና የኣማራ ኣስተሳሰብ የለበሱ) ግን እንዲሁ ዓይነቱ ኣባባል ሊዋጥላቸው ኣልቻለም።  ስለዚህ፣ ለነዚህ ልሂቃን በኢትዮጵያ የበላይነት መጠበቅ የሚቻል የትግራይ ህዝብ በማጥፋት ነው የሚል መስመር ያዙ። ኣንዳርጋቸው ጽጌ ከተባለ ሰው፣ ከኣንድ ምሁር የሚባል የማይጠቀብ የዘር ማጥፋት ሃሳብ በቅርቡ የሰነዘረው ለብዙ በሰብኣዊ ድህነት  የሚቆሮቆሩ ሰዎች ኣስደንግጠዋል።

ኣንዳርጋቸው ጽጌ የኣንድ የፖለቲካ ድርጅት የበላይ ኣባል እንድመሆኑ መጠን፥ የሰነዘረው የዘር ማጥፋት ሃሳብ የድርጅቱ መርገጫ ኣንደሆነም ኣየጠራጥርም። የሱ ድርጅት፥ ከኣብይ ኣህመድ የብልጽግና ድርጀት ተቈራኝቶ ስለሚሰራ፡ የብልጽግና ኣስተሳሰብ እንደሆነም ከጠቅላይ ምኒስትሩ ተመሳሳይ ኣዘግናኝ የዘር ማጥፋት ቃላት ወጥተዋል። ኣቢይ ኣህመድ፡ የትግራይ ህዝብ ኣረም እና የኢትዮጵያ ካንሰር በመሆኑ ተነቅሎ መጥፋት ኣለበት ኣለ። ከኣንድ የኣገር መሪ የሚባል ሰው እንዲህ ዓይነት ቃላት ሲወጡ እጅጉም የሚያስደነግጥ ነው።

ኣንዳርካቸው ጽጌ እና መሰሎቹ የኢሃድግ መንግስት በመቃወም የትጥቅ ትግል ያካሄዱ የኣንድ `ጁንታ` ኣባላት

ነበሩ። የሚግረው ነገር፡ ይህ ጁንታ በኤርትራ ነጻነት እምነት አልነበረውም፡ ግን ደግሞ ኤርትራ ባለው ዲክታተራዊ ስርዓት ነበር የትግል ትጥቅ ያገኝ የነበረው። ለመጥቀስ ያህል ነው እንጂ ይኽ ጉዳይ ከያዝነው መስመር ስለሚያስወጣን የተለየ ኣትኩሮ ኣርገን ብሌላ ኣጋጣሚ ኣንመለሰበታለን ።

ስለ ኣቢይ ኣህመድ ብዙ ሊባሉ የሚገባቸው ነገሮች ኣሉ። የሚረባ ሰው ኣይደለም፥ የማይረባ ተብሎ ብቸለልትነት የሚታለፍ ሰው ግን ኣይደለም። በመዋሸት እና በማደናገር ችሎታው ነው ስልጣን ለይ ሊውጣ የቻለው። ፍቅር እና መደመር የሚሉ የመታለያ ሃሳቦች ተጠቅሞ ምስኪኑ የትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ዓልምም ጭምር ለማሳመን ችለዋል። ሰላም በሌለበት ከኤርትራ ሰላም እንደተደረገ ተቆጥሮ የኖቤል ሽልማት ሊያገኝ የቻለ ኣደገኛ ሰው ነው።

### ለማጠቃለል ያህል

ስለ ኣቢይ ኣህመድ እዚህ ብዙም መናገር ኣያስፈልገንም፡ በይፋ የተገልጡና ብዙ የሚታወቁ ነገሮች ስላሉ። ሊባል የሚገባው ነገር ቢኖር፥ ኢትዮጵያ በማይቀረው የዩጎዝላቭያ እጣ በመጀመርያ በሃላፊነት ሊጠየቅ የሚግባው ሰው ኣቢይ ኣህመድ ነው። የስልጣን ስስት ያለው ሰው ስለሆነ የተወሰኑ የኢትዮጵያ ልሂቃን የቍጭት ማውጫ ሃሳባቸው ተቀብሎ የትግራይን ህዝብ ለማጥፋት ተነስተዋል። ለስልጣን ሲል ሲያስፈልገው ክርስትያን ነኝ ባዪ፣ ኣረቦች ኣገር ሄዶ የእስልምና ተከታይ መሆኑን የሚያወራ ሰው እኮ ነው። ስለዚህ፥ ኣብይ በማነኛውም ነገር፥ በሃይማኖት ወይም በዘር፡ በሆነ መንገድ የሚል የስልጣን ኣምልኮት ያለው ኣደገኛ ሰው ነው። በዓለማችን በዘር ማጥፋጥ የሚታወቁት ኣምባ ገነኖች፣ የኣቢይ ኣህመድን ዓይነት ኣስተሳሰበ እንደነበራቸው መገንዘብ ያስፈልጋል።

እንደ ኣንዳርጋቸው ጽጌ ዓይነቶች ብእጅ ኣዙር በገዛ ህዝባቸው ላይ ጉዳት ጫሪዎች መሆናቸው ጥቂቶች ልሂቃን ነገሩ ገብቶኣቸው ደፍረው መናገር ጀምርዋል። ኣገርዋ ብትበተንም፣ ትግሬዎች እና ኣማሮች ብጂኦግራፊያዊ ጉርብትና ነዋሪዎች ስለሆኑ ኣስተዋሊዎች የኣማራ ምሁራን የህዝባቸውን የማንቃት ስራ በሰፊው ልይዙት ይገባል። ይኽ ለማድረግ የእነኣንዳርጋቸው ጽጌና መሰሎቹ ኣስተሳሰብ ጸረ ጥቅማቸው መሆኑ ተገንዝበው፡ የኢትዮጵያ ደግ ኣሳቢ ልሂቃን ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ግዴታቸው ይሆናል።

ትግራይ ህዝብ ላይ የተፈጸመው የዘር ማጥፋት ዘመቻ፣ ይባስ ብሎም የውጭ ኣገሮች ጦር ሰራዊት ብማሳተፍ፡ ኣንድነቱ ኣንዲጠናከር ኣርጎታል። ከንግዲህ ወዲህ ትግራይ የኢትዮጵያ ኣካል ሆና ትቀጥላለች ብሎ ማሰብ የዋህነት ብቻ ነው የሚሆኖው ። ቢኢሃደግ የተከለለው የፈደራል ኣስተዳደር በእነ ኣንዳርካቸው ጽጌ መሰሎች ልሂቃን ግፊት ሞኙ ኣቢይ ኣህመድ ለማፍረሱ እየጣረ ነው። የኦሮሞ ህዝብ ድሮም ብጭቆና የኖረ ህዝብ ነው ኣሁን ደግሞ የራሱን የማስተዳደር መብቱ ሲነጠቅ እሰይ ብሎ የሚቀበለው ኣይሆንም። ስለዚህ ትግራይና ኣሮሞ ተባብረው በሚያደርጉት ግፊት ነው ለኢትዮጵያ መበታተን እውን የሚያደርገው፣

የኢትዮጵያ መበታተን ግን የሚይስደነግጥ ስይሆን ለቀርን ኣፍሪቃ የሚባለው ሁሉ እንዲያው ዘላቂ ሰላም የሚያመጣ ሊሆን ይችላል። ኢትይጵያ የምትባል ሰፊ ኣገር በሰላም ተግዝታ ኣታውቅም ህዝቦችዋም ከድህነት ቍራኛ መውጣት ኣልቻሉም። በመበታተን፡ ነጻ ትግራይ፥ ነጻ ኦሮሞ፥ ነጻ ኣማራ ወዘተ ኣገራት ሲቋቋሙ ግን የበለጠ ዘላቂ ሰላም ለመምጣት ስለሚቻል፡ የህዝቦቻቸው ኑሮም በዘ መንጽር የእድገት ተስፋ ይኖሮዋል። እንዲሁ ዓይነት ሁኔታ ለኤርትራና ሌሎች የቀርን ኣፍሪቃ ኣገራትም ጭምር ዘላቂ ሰላም ሊያስመጣ እንደሚችል ለመገመት ኣያዳግትም።

ለተፈጸመው ኣዘግናኝ የዘር ማጥፋት ዘመቻ እና በሰው በደረሰው እልቂት ባሃላፊነት በፍርድ ቤት ስለሚጠየቁ ግለ ሰዎች በተመልከ ግን ለህግ ባለሞያዎች መተዉ መርጠናል።

በመጨረሻ፡ እዚህ ድርሰት ወስጥ የተጠቀሱ ሃሳቦች ሙላት ያላቸው እንዳልሆኑ ግልጽ ነው ስለዚህ የታሪክ/የፖሊቲካ ምሁራን በስፋት ተመራምረው የሚያጠግብ መደምደምያዎች እንድያደርጉ ተስፋችን ነው። ለምሳሌ፥ በኣጼ ምንሊክ መሪነት የተካሄደው የኣድዋ ጦርነት ድል ያስገኙት ኣንድ የኤርትራ ተወላጅ ሰላይ ክትግራይ ሰራዊት በመተባበር ሁኖ ሳለ ሆን ተብሎ ታሪኩ ኣንዲቀበር ተደርገዋል የሚሉ ኣሉና ማጣራት ያስፈልግዋል። እንዲሁም፣ ኣጼ ቲድሮስ ከነ ኣካቴው የትግራይ ተወላጅ ናቸው ይባላል። ሊሆን ይችላል፣ ብምርምር የታገዘ ማስረጃ ባለመኖሩ።

ተፈጸመ።